MINNESOTA
FRONTLINE WORKER PAY

# የሚኒሶታ የፊት መስመር የሰራተኛ ክፍያ

## ስለ



ኮቪድ (COVID-19) ለመቋቋም በተደረገው ትግል በግንባር ቀደም ተሰልፈው ያገለገሉትን ሁሉ ለማመስገን፤ አገረ-ገዢ ቲም ዋልዝ (Gov. Tim Walz)፤ ሰራተኞች የግንባር ቀደም ክፍያ ወይም ካሳ- ፍሮንትላይን ወርከር ፔ (Frontline Worker Pay) እንዲያገኙ የሚያስችላቸውን ህግ ሚያዝያ (April) 29 ቀን 2022 እንዲጸድቅ ፊርማቸውን አሰፈሩ። የዚህ ፕሮግራም ዝርዝር እንዲሁም የማመልከቻውን ሂደትና ክፍያው የሚሰጥበትን ግዜ የሚያስረዳ መረጃ በኦንላይን በ frontlinepay.mn.gov. ይገኛል። ዌብሳይቱን በመጎብኘት ስለዚሁ የፍሮንትላይን ወርከር ፔ (Frontline Worker Pay) በ ኢሜል አስፈላጊውን መረጃ ለማግኘት ይፈርሙ።

## ብቁ የሆነው ማነው

ይህንን ክፍያ/ካሳ ለማግኘት ብቁ መሆናቸውን የሚያሳዩ ሁለት ቀደምት ክፍሎች አሉ- የስራ ጥያቄና የስራ ዓይነት።

## የስራ ጥያቄ

ለዚሁ ለግንባር ቀደም ሰራተኛ ክፍያ፤ አመልካች:

- በሚኖሶታ ውስጥ፤ በግንባር ቀደም ስራ፤ ቢያንስ 120 ሰዓታት የሰራ መሆን አለበት። ይህም ከመጋቢት (March) 15 ቀን 2020 እስከ ሰኔ (June) 30 ቀን 2021 መሆን አለበት።
- በእነዚህ በሰራባቸው ሰዓታት፤ አመልካቹ –
  - በሚሰራባቸው ሰዓታት ዋነኛውን ስራውን በስልክ ማካሄድ( telework) ያልቻለ መሆን አለበት
  - ከግለሰቡ መኖርያ ቤት ውጭ ካሉ ሰዎች ጋር በቅርብ እየተገናኘ መስራትን
- ቢያንስ የ2020 ወይም የ 2021 የግብር ዓመታት የሚጠይቀውን የገቢ ክልል ማሟላት –
  - የኮቪድ (COVID-19) በሽተኞች እንክብካቤ ቀጥታዊ ሓላፊነት ያላቸው ሰራተኞች ያገቡና ግብር የሚከፍሉ ከሆነ ገብያቸው* ከ$350,000 በታች፤ ሌሎች ደግሞ ከ$175,000 በታች መሆን አለበት።
  - የኮቪድ (COVID-19) በሽተኞች እንክብካቤ ቀጥታዊ ሓላፊነት የሌላቸው ሰራተኞች ያገቡና አንድ ላይ ግብር የሚከፍሉ ከሆነ ገብያቸው* $185,000 መሆን አለበት፤ ለሌሎች ደግሞ ከ$85,000 በታች መሆን አለበት።
- ከ መጋቢት (March) 15 ቀን 2020 እስከ ሰኔ (June) 26 ቀን 2021 ከስራ የመውጣት ክፍያ (unemployment insurance benefit) ከ20 ሳምንታት በላይ በተከታታይ ያላገኘ መሆን አለበት።

*ስለ ተጨማሪ የገቢ ማሻሻያ ሁኔታ፡ በ irs.gov/e-file-providers/definition-of-adjusted-gross-income ይመልከቱ።

MINNESOTA

ግንቦት (May) 2022

## የስራ ዓይነቶች

1. የህንጻ ስራ፣ ማደስ፤ የጽዳትና የደህንነት አገልግሎት
2. የልጅ እንክብካቤ
3. ፍርድ ቤቶችና ማረምያ ቦታዎች
4. የአስቸኳይ/ድንገተኛ አደጋ ተቋቋሚዎች
5. የምግብ አገልግሎት፡ የምግብ ምርት፤ ዝግጅት፣ ገበያና ማደራረስ ጭምር
6. የመሬትና የአየር የማመላለሻ አገልግሎቶች
7. የጤና ጥበቃ ስራ
8. የረጅም ግዜ ና የቤት ውስጥ እንክብካቤ
9. ፋብሪካዎች
10. የህዝብ ጤንነት፣ ማህበራዊ አገልግሎት፣ የመቆጣጠርያ አገልግሎት
11. የህዝብ ማመላለሻ
12. የንግድ ስራ፣ ማሰራጨትና ማድረስ
13. ትምህርት ቤቶች፣ ቻርተር (charter schools) ትምህርት ቤቶች፤ የመንግስት ትምህርት ቤቶችና ከፍተኛ ትምህርት የሚሰጥባቸው ጭምር
14. ግዜያዊ መጠለያዎችና ሆቴሎች እና
15. የሞያ መልሶ ማቋቋምያዎች

## የት ማመልከት እንደሚቻል

ማመልከቻው ከተዘጋጀ በኋላ፤ ብቁ የሆኑ ሰራተኞች የግንባር-ቀደም ክፍያ (Frontline Worker Pay) ለማግኘት፤ በኦንላይን ወደ frontlinepay.mn.gov. ገብተው ለማመልከት የ45 ቀናት ግዜ ይሰጣቸዋል። ጠቃሚ መረጃዎችን ለማግኘት ለምሳሌ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች መልስ ፣ በብዙ ቋንቋዎች የተተረጎሙ ጽሁፎችንና እንዴት ማመልከት እንደሚችሉ የሚያግዙ ቪድዮዎችን እንዲሁም ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት ዌብሳይቱን ይጎብኙ።

## ማመልከቻውን ለመረዳትና ለመሙላት የሚደረግ እርዳታ

የማመልከቻው ፎርም ከተጠናቀቀ በኋላ፤ የእርዳታ ሰጪ ክፍሉ፤ አምልካቾች በአያሌ ቋንቋዎች እርዳታ እንዲያገኙ ያደርጋል።

## ክፍያዎች

የማመልከቻው ሂደትና ማረጋገጫዎች ከተጠናቀቁ በኋላና ምናልባት ተቀባይነት ያላገኙ አመልካቾች ስለጉዳያቸው መከራከርያ የ 15-ቀናት ግዜ ከተሰጣቸው በኋላ፤ የአመልካቾች ጉዳይ የመጨረሻውን ውሳኔ ያገኛል። እያንዳንዱ ብቁ የሆነ አመልካች፤ ከሌላው ጋር አንድ ዓይነት ክፍያ ያገኛል። ሁሉም ማመልከቻዎች አንድ ላይ በአንድ ግዜ ይታያሉ፤ ክፍያውም ለሁሉም በአንድ ግዜ ይሰጣል።

*ማስታወሻ፡ ይህ በራሪ ወረቀት የሚኖሶታ ህግን በአጭሩ የሚገልጽ ነው። እንደ አንድ መመርያ እንዲወሰድ እንጂ የሚኖሶታ የግንባር ቀደም የሰራተኞች ክፍያን (Frontline Worker Pay) ለመተካት የተደረገ አይደለም።*

MINNESOTA

ግንቦት (May) 2022